# የጌታ ራት

ከአማረ መስፍን

## 1 ታሪካዊ ዳህራይ መሠረት

የጌታን ራት አስመልክቶ ተቋማዊ ድንጋጌውን በወንጌላት ውስጥ የምናገኝ ሲሆን (ማቴ 26፥26-29፣ ማር 14፥22-25፣ ሉቃ 22፥14-20) አስተምህሮውን ግን የምናገኘው በመልእክቶች ውስጥ ነው (1ቆሮ 11፥17-34)።

ስለ ጥምቀት በተሰጠው ኖት ላይ እንደተብራራው በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ጥምቀትና የጌታ ራት ያሉ ሥርዐቶች ምሥጢራት (Mysterion) ይባሉ ነበር። እንደ ግሪክ ኦርቶዶክስ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ዛሬም በዚሁ መጠሪያ ይጠራሉ። ኢየሮኒሞስ (የሮም) የተባለው የቤተ ክርስቲያን አባት "Mysterion" የሚለውን ቃል "Sacramentum" (ቅዱስ ሥርዐቶች) በሚለው የላቲንኛ ቃል ስለተረጐመው የላቲኗ (የምዕራቧ) ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሥርዐቶች ቅዱስ ሥርዐቶች ወይም ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በማለት ትጠራቸው ነበር።[1]

የእነዚህን ሥርዐቶች ባሕርይ አስመልክቶ የጠራ አስተምህሮን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስቀመጠው አውግስጢኖስ ሲሆን ሥርዐቶቹን “የማይታየው ጸጋ ወይም መለኮታዊ ባርኮት የሚታዩ ምልክቶች ናቸው” በማለት ሰይሟቸዋል። ስለዚህ በእነዚህ ቅዱስ ሥርዐቶች ውስጥ ሁለት ነገሮች ዐበይት ናቸው፤ ውጫዊ የሆነው፣ ስሜት የሚሰጠውና የሚታየው ምልክት (The *signum* - sacramentum in the stricter sense) እና ውስጣዊ የሆነው፣ የማይታየውና ከእምነት ጋር የተያያዘው ጸጋ ወይም መለኮታዊ ባርኮት (The *res*, also *virtus sacramenti*)

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምንም ጥምቀትና የጌታ ራት ተቀዳሚ የሆኑ ቅዱስ ሥርዐቶች ተደርገው ይወሰዱ የነበረ ቢሆንም፤ “ቅዱስ ሥርዐቶች” (ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን) ተብለው የሚጠሩ ሌሎችም አያሌ ክርስቲያናዊ ልምምዶችና ሥርዐቶችም ነበሩ። ለምሳሌ በ12ኛው ምዕተ ዓመት ግድም ቀዳማይ ከሚባሉት የጀርመን ነገረ መለኮታውያን አንዱ የቅዱስ ቪክቶሩ ሁን “ቅዱስ ሥርዐቶች የማይታየው ጸጋ የሚታዩ ምልክቶች ናቸው” የሚለውን የአውግስጢኖስን አስተምህሮ መሠረት በማድረግ የቅዱስ ሥርዐቶቹን ቊጥር ወደ 30 አድርሷቸው ነበር። ሆኖም በ1545 ዓ.ም. ትሬንት ላይ የተሰበሰበው ጉባኤ ቅዱስ የሚመስሉ ሥርዐቶች በሙሉ የቅዱስነት ዋጋ ሊሰጣቸው አይገባም በማለት ደንግጓል።

በመቀጠልም የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሥርዐቶቿን ወይም የምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ቊጥር ሰባት መሆናቸውን የወሰነች ሲሆን፤ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተነሡት ተሐድሶአውያን ግን ይህ ቊጥር የተወሰነው ያለ አግባብ መሆኑን በመግለጽና የቃሉን ፍቺ በሚገባ በመተንተን ቅዱስ ሥርዐቶች ማመልከት ያለባቸው የማይታየውን ጸጋ የሚያመለክቱትን የሚታዩ

[1] Achtemeier, P. J., Harper & Row, P., & Society of Biblical Literature.. *Harper's Bible dictionary.* (1st ed.). Harper & Row: San Francisco 1985; P 890

ምልክቶች ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንዲፈጸሙ ያዘዛቸውን ትእዛዛት ነው በማለት አስተምረዋል። ይህ ደግሞ የሥርዐቶቹን ቍጥር ወደ ሁለት ዝቅ ያደርገዋል።

በዘመናችን ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ያለው የቃላት አጠቃቀም በአብዛኛው በሁለት ይከፈላል። አንደኛው እንደ ካቶሊክ እና ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ያሉት የሚጠቀሙበት ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን (Sacraments) የሚለውና ምስጢራቱ ጸጋን ሊያስተላልፉ ይችላሉ የሚለውን አስተምህሮ ታሳቢ ያደረገ አጠቃቀም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአብዛኞቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ጥቅም ላይ የዋለው የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶች ወይም ትእዛዛት (Ordinances) የሚለው ነው። ሆኖም አንዳንድ እንደ ሉተራን፣ አንግሊካንና ወዘተ ያሉ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትም ምስጢራቱ ጸጋን ሊያስተላልፉ ይችላሉ የሚለውን ታሳቢ ባላደረገ መልኩ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ።

## 2. የስያሜ ትርጕም

የሥርዐቱን ስያሜ በሚመለከት የተለያዩ ቤተ እምነቶች ለሥርዐቱ ካላቸው አተረጓጐም የተነሣ የተለያየ አጠራርን የሚጠቀሙ ሲሆን ዐበይት የሆኑትን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፦

### 2.1 ቅዱስ ቍርባን Holy Communion

ሥርወ ቃሉ “በጋራ መካፈል” የሚል ትርጕም የሚሰጠው የላቲንኛ ቃል "Communio" ነው። የሐሳቡ መነሻ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 10፥16 ላይ “የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?” በማለት የጻፈው ሲሆን[2] በዚህ ክፍል ውስጥ “ኅብረት” የሚለው ቃል ደግሞ በግሪክኛው “κοινωνια” (koinonia) ኅብረት፣ ሱታፌ፣ አጋርነት የሚል ትርጕም አለው።[3]

እንደ ካቶሊክ እና ኦርቶዶክስ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የኅብስቱና የወይኑን በቀጥታ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም መለወጥ አስመልክቶ ካላቸው አስተምህሮ በመነሣት ሥርዐቱን ቅዱስ ቍርባን ወይም ሥጋ ወደሙ በማለት ይጠሩታል። በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እምነት ቅዱስ ቍርባኑ የሚያመለክተው አጠቃላይ ሥነ ሥርዓቱን ሳይሆን ኅብስቱንና ወይኑን ብቻ ሲሆን አንድ ሰው ሥርዐቱን ተካፍሎ የተቀደሰውን ኅብስትና ወይኑን (ሥጋ ወደሙን) ላይወስድ ይችላል።

በተሃድሶአውያኑ (ሉተር፣ ካልቪን፣ ዝዊንግሊ እና ወዘተ...) አመለካከት ግን ቃሉ ባጠቃላይ ሥርዐቱን የሚወክል ሲሆን እንደ ካቶሊክና ኦርቶዶክስ አማኞች ኅብስቱና ወይኑ ይለወጣል የሚል አመለካከት ስለሌላቸው ብዙዎቹ የፕሮቴስታንት አማኞች “ቅዱስ ቁርባን” የሚለውን ትተው “የጌታ ራት” የሚለውን ይጠቀማሉ።

[2] Howard Marshal, *Last Supper and Lord's supper* The Paternoster Press, Carlisle, UK; 1980, P. 15
[3] Strong # 2842

### 2.2 ምስጋና ማቅረብ Eucharist

ቃሉ በግሪክኛ "εὐχαριστία" (Eucharistia) ሲሆን በእንግሊዝኛ "Thanks giving" ምስጋናን ማቅረብ ማለት ነው። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 26፥26-27 ላይ ማዕዱን ከባረከበት የበረከት ቃል በመነሣት የተሰጠ መጠሪያ ነው። ቃሉም ከሥርዐቱ አንዱ ክፍል ስለነበረው ምስጋና ማቅረብ የሚናገር ነው። ማር 14፥23፤ ሉቃ 22፥17-19፤ 1ቆሮ 11፥24።

ይህ ቃል በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በጣም የተለመደና በተለይም በምሥራቃውያኑ ዘንድ በስፋት ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ሲሆን፤ ዮሐንስ አፈወርቅ "ለቤዛነቱ በረከት የሚቀርብ ክቡር የሆነ ምስጋና ነው" ስላለ የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ስያሜውን ትጠቀምበት ነበር[4]። በአሁኑ ዘመን ካቶሊክ፣ ምሥራቃዊቷ ኦርቶዶክስ፣ አንግሊካን፣ ዩናይትድ ሜቶዲስቶችና አንዳንድ ሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት ይጠቀሙበታል።

### 2.3 እንጀራን መቁረስ Breaking of bread

ከአንዳንድ ምንባባት እንደምንረዳው ሐሳቡ ምግብንም ከመመገብ ጋር የተያያዘ አገላለጽ ያለው ቢመስልም (ሉቃ 24፥35፣ ሐዋ 2፥42)፤ የጌታ ራትንም ለመግለጽ የዋለ ቃል እንደሆነ ደግሞ ከሌሎች ምንባባት እናያለን ሐዋ 20፥7፣ 1ቆሮ 10፥16።

### 2.4 የጌታ ራት The Lord's Supper

ይህ ቃል በተለይ በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በስፋት በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ሥርዐቱን ባጠቃላይ የሚወክልና በአተረጓጎምም ደረጃ የሥርዐቱን ማስታወሻነት ብቻ አጉልቶ የማሳየት አቅጣጫን የያዘ ቃል ነው 1ቆሮ 11፥20-26።

## 3. የፋሲካ ራት እና የጌታ ራት

### 3.1 የአይሁድ የፋሲካ በዓል

በዕብራይስጡ פֶּסַח (*pesach*) ሲሆን የቃሉ ትርጉም አንድን ነገር ሳይነኩ ማለፍ፣ በላዩ ላይ ማለፍ እንደማለት ነው።[5] አይሁድ በዋነኛነት ከሚያከብሯቸው በዓላት ውስጥ፤ የመቅደስ በዓላቱ ዑደት በፋሲካ በዓል ይጀምርና በቂጣ በዓል ይቀጥላል። እነዚህ ሁለት በዓላት የተለያዩ በዓላት ነበሩ (ዘሌ 23፥5-6 ዘኁ 28፥16-25፣ 2ዜና 30፥15, 21፣ ዕዝ 6፥19-22፣ ማር 14፥1)

የፋሲካው በዓል በአይሁድ ሃይማኖታዊ የቀን መቁጠሪያ መሠረት የሚውለው በአቢብ (ኒሳን) ወር (የመጀመሪያው የአይሁድ ወር በእኛ አጠራር ሚያዚያ) በ14ኛው ቀን ሲሆን (ዘፀ 12፥1-6፣ ዘኁ 9፥1-5)፤ የቂጣ በዓል ደግሞ በዚሁ ወር ከ15ኛው ቀን አንስቶ እስከ 21ኛው ቀን ድረስ ይከበር ነበር (ዘፀ 12፥15)። ከዚህ የተነሣ በተለይ በሐዲስ ኪዳን ዘመን በአንድነት ይከበሩ ነበር (ማቴ 26፥17፣ ማር 14፥12፣ ሉቃ 22፥1)።

---

[4] Charles Hodge, *Systematic Theology* Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor, WA, 1997, Vol. 3, Page 613

[5] Swanson, J. *Dictionary of Biblical Languages with Semantic Domains : Hebrew (Old Testament)* . Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor1997 # 7175

## 3.2 የአዲስ ኪዳኑ የፋሲካ በዓል አከባበር

የፋሲካውን በዓል እና የቂጣውን በዓል አጠቃላይ አከባበር አስመልክቶ በሦስቱ ወንጌላት እና በዮሐንስ ወንጌል መካከል መጠነኛ ያለመግባባት ይታያል:: ሦስቱ ወንጌላት ማለትም ማቴ 26፥17-19፣ ማር 14፥12-16፣ 15፥1-15፣ ሉቃ 22፥7-16 ኢየሱስ ክርስቶስ በዓሉን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ካከበረ በኋላ ወደ ስቅላቱ እንደሄደ ሲናገሩ፤ (ሉቃስ ከሞቱ በፊት ይህን ፋሲካ ከእነርሱ ጋር ለመብላት ይመኝ እንደነበረም ዘግቧል ሉቃ 22፥15)::

የዮሐንስ ወንጌል ግን ከሦስቱ ወንጌላት ትረካ ለየት ባለ መልኩ የፋሲካው በዓል የተገጣጠመው ከኢየሱስ ስቅለት ጋር እንደነበር ጠቅሷል (ዮሐ 13፥1-20፣ 18፥28፣ 19፥14):: ከዮሐንስ ሐሳብ ለመረዳት የምንችለው ዮሐንስ በወንጌሉ ላይ የፋሲካውን በግ ተምሳሌትነት ከኢየሱስ መሥዋዕትነት ጋር ለማያያዝ እንደፈለገ ነው:: ይህ ደግሞ ኢየሱስና ደቀ መዛመርቱ የፋሲካን ራት እንዳልበሉ የሚያስገነዝብ ይሆናል::

## 3.3 የማጠቃለያ ሐሳብ

### 1ሀ የፋሲካ በዓል የብሉይ አከባበር

የፋሲካ በዓል በመጀመሪያው ወር (አቢብ/ኒሳን) በ14ኛው ቀን ጸሓይ ስትጠልቅ ወይንም ሲመሽ ጀምሮ ይከበራል ዘፀ 12፥6

- ደሙን ወስደው የሚበሉበትን ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቀቡታል
- በእሳት የተጠበሰውን ሥጋና የቂጣውን እንጀራ ከመራራ ቅጠል ጋር ይበሉታል
- እስኪነጋ ድረስም አንዳች ሳያስቀሩ ይበሉታል፤ ከቀረም ማልዶ ይቃጠላል
- በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ደሙ ያልተቀባውን የግብፃውያን ቤት በመቅሰፍት ይመታል፣ ደሙ ያለበትን ያልፋል (እንደ ቃሉ ትርጉም) ስለዚህ መታሰቢያነቱ ለሕዝቡ ከመቅሰፍት መጠበቅ ነው ዘፀ 12፥27

### 2ሀ የቂጣ በዓል የብሉይ አከባበር

የቂጣ በዓል በመጀመሪያው ወር (አቢብ/ኒሳን) ከ15ኛው ቀን ጀምሮ ለሰባት ቀናት በተከታታይ ይከበራል ዘፀ 12፥15-20፣ ዘኍ 28፥17-25፣ ዘሌ 23፥4-8

- በመጀመሪያው ቀን እርሾን ባጠቃላይ ከቤታቸው ያስወጣሉ፤ ለሰባቱም ቀናት እርሾ ያለበትን ምግብ አይበሉም፤
- የመጀመሪያውና የሰባተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ስለሚሆን ከመብላት በቀር ሥራን አይሠሩም፤
- መታሰቢያነቱ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ያወጣበት ቀን ስለሆነ ያንን ለመዘከር ነው፤
- በዚህ በዓል ላይ ያልቦካ እንጀራን የሚበሉበት ምክንያት በዘፀ 12፥34, 39፣ 13፥3 መሠረት ከግብፅ ተቻኩለው መውጣታቸውን ለማስታወስ ነው::

### 3ሀ ከአዲስ ኪዳኑ አከባበር ጋር ስናስተያየው

በብሉይ ከሁለቱ በዓላት ቀዳሚ የነበረው ሥርዐት የፋሲካው ራት ሲሆን የሚከናወነውም ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ምክንያቱም በነጋታው ከ15ኛው ቀን ጀምሮ የሚውለው የቂጣ በዓል ሥርዐት ይጀመራል::

ስለዚህ ምንም ሦስቱ ወንጌላት የፋሲካን በዓል ከቂጣ በዓል ጋር አቀላቅለው ቢያቀርቡትም ጳውሎስ በ1ቆሮ 11፥23-32 ላይ የተናገረውን ሐሳብ ጨምረን ጉዳዩን ስናየው፦

- ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት እንዳከበረ
- ሆኖም በዚሁ ሥርዐት ላይ የሥጋውና የደሙ መታሰቢያ የነበረውን አዲስ የመታሰቢያ ሥርዐት እንደደነገገ
- የኢየሱስ ስቅላት ከፋሲካው ራት በኋላ እንደነበር ለመረዳት እንችላለን።

# 4. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህር

## 4.1 የጌታ ራትን አስመልክቶ የተሠነዘሩ የተለያዩ አመለካከቶች

ክርስቲያን በሚለው ሰፊ ጃንጥላ ሥር ተጠልለው የሚገኙ በቍጥር እጅግ ብዙ ቤተ እምነቶች ሥርዐቱ መፈጸም እንዳለበት የጋራ የሆነ አቋም ያላቸው ሲሆን፣ ሥርዐቱ ለድነት ባለው አስተዋጽኦ፣ በስያሜው፣ በአፈጻጸሙ፣ በተቀባዮቹ፣ በአዘገጃጀቱና በመሳሰሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ግን የተለያየ አመለካከት አላቸው።

### 1ሀ የሮማ ካቶሊክ አመለካከት (ውሳጢ) TRANSUBSTANTIATION

"Transubstantiation" የሚለው ቃል የሚተረጐመው "Transsubstantiatio" የሚለውን የላቲን ቃልና "metousiosis"[6] የሚለውን የግሪክኛ ቃል ሲሆን ቃላቱ ባጠቃላይ በሥርዐቱ ወቅት የሚቀርቡትን ኅብስትና ወይን መቀየር ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ናቸው።

የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፣ የምሥራቁ፣ የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ እና የምሥራቋ ሶርያዊት ቤተ ክርስቲያናት ለአማኞች የሚቀርቡት ኅብስቱና ወይኑ ጣዕማቸው፣ መልካቸውና ቅርጻቸው[7] ሳይቀየር በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት በትክክል፣ በእውነትና መሠረታዊ በሆነ ሁኔታ ይቀየራሉ የሚል አስተምህሮን ይከተላሉ።

ካቶሊካዊትም ሆነ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የሚጠቀሙበት ቃል “ቅዱስ ቍርባን” የሚለውን ሲሆን ሥርዐቱንም ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ብለው ከሚጠሯቸው ምስጢራት ውስጥ እንደ አንዱ ተቀብለውታል። ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን (Sacraments) በማለት የምትቀበላቸው ሥርዐቶች ጥምቀት፣ አንብሮተ እድ፣ ቅዱስ ቍርባን፣ ንስሓ፣ ሢመት፣ ቀንዲል እና ተክሊል ናቸው። ይህንንም በ1545 እ.ኤ.አ. የትሬንቱ ጉባኤ ነበር ያጸደቀው። በሌላው መልኩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በማለት የምትቀበላቸው በሁለት ክፍሎች የሚከፈሉ ሲሆን፦

#### 1ለ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት

አዕማድ የግዕዝ ቃል ሲሆን የአምድ ብዜት ቃል ነው በትርጕምም ምሰሶዎች ወይም ዋና ቋሚዎች እንደ ማለት ነው። አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሥጢረ ሥላሴ፣ ሥጋዊ፣ ጥምቀት፣ ቍርባን፣ እና ትንሣኤ ሙታን ናቸው። እነዚህም ዶግማ (መሠረተ እምነት) ተብለዋል የቤተ ክርስቲያኒቱም የእምነት መሠረቶች ናቸው።

---

[6] Metousiosis = A change of "ousia" (essence or inner reality)
[7] ለዚህ አባባል በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ሙያዊ ቃል "Accidents" የሚል ነው።

## 2ለ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቍርባን፣ ክህነት፣ ተክሊል፣ ንሥሐ እና ቀንዲል

በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ መሠረት እነዚህ ምሥጢራት በክርስቶስ መሥራችነት የተመሠረቱና በእነርሱም አማካይነት እግዚአብሔር ጸጋውንና ጽድቁን የሚሰጥባቸው ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ምሥጢራት ክርስቶስ ራሱ በዕለተ ዓርብ ካደረገው የማዳን ሥራ የመነጨ፣ ኀይሉ የሚታወቅባቸው፣ ሥልጣኑ የሚገለጥባቸው፣ የማንጻትና የማጽናት ሥራው የሚታይባቸው ታላላቅ ምሥጢራት ሲሆኑ፤ ካህኑ ደግሞ የማንጻት ተግባር የሚፈጽምባቸው የእግዚአብሔርን ጸጋና ሀብት ልጅነትንም የሚያስተላልፍባቸው የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገለጥባቸው ናቸው የሚል አስተምህሮ አላት::

ከሰባቱ ውስጥ አራቱ የግድ ለማንኛውም ሰው አስፈላጊ ናቸው (ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቍርባን፣ ንሥሓ) ያለ እነዚህ ድነትን ማግኘት ስለማይቻል፤የተቀሩት ሦስቱ (ክህነት፣ ቀንዲል፣ ተክሊል) ለፈለገ ሰው ብቻ የሚሆኑ ናቸው:: ተደጋግመው መፈጸም ያለባቸው ቍርባን፣ ንሥሐ፣ ቀንዲል ሲሆኑ፤ የማይደጋገሙ ደግሞ ክህነት፣ ጥምቀት እና ሜሮን ናቸው:: ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ይለወጣሉ የሚለው አስተምህሮ 3 ችግሮች አሉበት:-

1) **የክርስቶስን መሥዋዕትነት ማጓደል**
ክርስቶስ ለሰው ልጆች በሙሉ የከፈለው ዋጋ ያለ ምንም ተጨማሪ ማሟያ በራሱ በቂ ነው:: ዋጋውም የተከፈለው ገና ኀጢአተኞች ሳለን ሲሆን (ሮሜ 5፥6-8) የእኛ ሥርዐቶችን መፈጸምም ሆነ ያለመፈጸም በድነታችን ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ለውጥ የለም፤ ዋጋው ምሉዕና ፍጹም ነውና:: መጽሐፍ ቅዱሳችን ክርስቶስ ለሰው ልጆች የከፈለው ዋጋ ለአንዴና ለዘላለም የተከፈለና እገዛም ሆነ ጥገና የሚያስፈልገው እንዳልሆነ ነው የሚያስተምረን (ዕብ 10፥10-14)::
2) **የክርስቶስን ትእዛዝ በአግባቡ ያለመፈጸም**
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሥርዐት ሲመሠርት አማኞች ሥርዐቱን በፈጸሙ ጊዜ ሁሉ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች እንዲፈጽሙ እንጂ እርሱ የከፈለውን ክፍያ እንዲያግዙ አይደለም:: ስለዚህ ሥርዐቱን በመፈጸም የተለየ ጸጋንና በረከትን ለማግኘት ማሰብ ቃሉን በትክክል ያለመረዳት ይሆናል::
3) **ሥራና ጸጋን ማምታታት**
ከዳንን በኋላ የምንፈጽማቸው ክርስቲያናዊ ተግባራት በሙሉ ጌታ ራሱ “ብትወዱኝ ትእዛዜን ፈጽሙ” እንዳለ (ዮሐ 14፥15) ክርስቶስን ለመውደዳችን ማስረጃዎች እንጂ ድነታችንን ምሉዕ ለማድረግ የምናከናውናቸው እገዛዎች አይደሉም:: የዳንነው በጸጋው ሥራ በማመናችን እንጂ ሕግን በመጠበቅም አይደለም:: (ገላ 2፥16) በኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት የኅብስቱ የአቀራረስ ሥርዐት አለ:: ይህም በኦርቶዶክስ ሥርዐተ ፈትቶ ዘጽርስፎራ[8] የተባለ ራሱን የቻለ አስተምህሮ ያለው ነው::

[8] ፈትቶ የሚለው ቃል መፈተት፣ መቍረስ ወይም መግመስ ማለት ሲሆን (ኪዳነወልድ ገጽ 738)፤ ጽርስፎራ ደግሞ **προσφορά** (*prosphora*) ከሚለው የግሪክኛ ቃል የተገኘና መሥዋዕት ወይም ቍርባን ማለት ነው::

# ሥርዐተ ፈትቶ ዘጽርስፎራ




1. ከ 0 እስከ 1 = ክርስቶስ ከሰማይ ወደ ምድር መውረዱን (ርደት)
2. ከ 2 እስከ 7 እና ከ 7 እስከ 12 = ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ይሁዳ እና እስከ ኢየሩሳሌም መመላለሱን (አስተምህሮ)
4. ከ 12 እስከ 14 = የክርስቶስን መስቀል፣ ሞቱን፣ መቀበሩንና ወደ ሲኦል መሄዱን
5. ከ 14 እስከ 15 = ክርስቶስ ከሞት መነሣቱንና ዳግም በክብር እስኪመጣ ድረስ ማረጉን (ዕርገት)

ከላይ ከተሰጠው ማብራሪያ በተጨማሪ በስዕሉ ውስጥ ክርስቶስንና ሐዋርያቱን የሚወክሉ 13 መስቀሎች፣ በአንድ ኅብስት ውስጥ ራስ እና አባላት ተጠቃለው ይታያሉ (1ቆሮ 10፥14-17)::[9]

## 2ሀ የሉተራውያን አመለካከት (ቱሰሔ) CONSUBSTANTIATION

የካቶሊካውያኑን ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ይለወጣል የሚል አስተምህሮ ከተቃወሙት መካከል አንዱ ተሐድሶአዊው ማርቲን ሉተር ሲሆን የእርሱ ተቃውሞ ከሌሎቹ ተሐድሶአውያን ይልቅ ለዘብ ያለ አቋም ታይቶበታል:: ከሉተር የተቃውሞ ነጥቦች ሦስቱ ዐበይት ናቸው:-

### 1ለ የኅብስቱና ወይኑን መለወጥ አስመልክቶ ያቀረበው ተቃውሞ

በሉተር አመለካከት ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት አይለወጡም:: ነገር ግን ምሥጢራዊና ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ ጌታ በሁለንተናው፤ ከቍርባኑ ጋር፣ በቍርባኑ ሥር እና በቍርባኑ ውስጥ አለ::[10] ክርስቶስ ኅብስቱን በእጁ በያዘ ጊዜ ሥጋውንም አብሮ ይዞ ስለነበረ ነው "ይህ ሥጋዬ ነው" ያለው:: ስለዚህ ይህን ሥርዐት የሚካፈል ሁሉ አማኝ ቢሆንም ባይሆንም ኅብስቱን በተቀበለበት ቅጽበት ሥጋውንም ይቀበላል ማለት ነው::[11] ይህ የሉተር አስተምህሮ ከካቶሊካውያኑ አስተምህሮ እጅግም ልዩነት ያልታየበት ነበር፤ ምክንያቱም በዚህ አነጋገሩ የተቃወመው የኅብስቱና የወይኑን ቁስ አካላዊ ያለመለወጥ እንጂ በሥርዐቱ ውስጥ የክርስቶስን ሥጋና ደም መገኘትና አስፈላጊነት አምኗል:: ሆኖም የሥርዐቱን ጠቀሜታ አስመልክቶ የነበረው አቋም ብዙም ግልጽ አይደለም:: አንድ ሰው ይህን ሥርዐት ሲካፈል እውነተኛ የሆነ ጥቅምን ማለትም የእምነት ጽናትንና የኀጢአትን ይቅርታን ያገኛል፤ ሆኖም ይህን የሚያገኘው በኅብስቱና በወይኑ አማካይነት ሳይሆን ቃሉን በእምነት በመቀበል ነው የሚል አመለካከት ነበረው::[12] ስለዚህ ከሉተር አመለካከት የምንረዳው ሥርዐቱን ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንዱ መቀበሉንና አማኝ ይህን ሲካፈል የሚያገኘው መንፈሳዊ በረከት እንዳለ ነው::[13]

### 2ለ የኅብስቱና ወይኑ መሥዋዕት መሆን

ሉተር ሌላው የተቃወመው የካቶሊካውያን አስተምህሮ ቍርባኑ መሥዋዕት ነው የሚለውን ነው:: በሉተር አስተምህሮ ክርስቶስ አንዴና ለሁሉ በሚበቃ መልኩ የኀጢአትን መሥዋዕት እስካቀረበ ድረስና አማኙም ከዚህ መሥዋዕት የተነሣ በእምነት እስከ ጸደቀ ድረስ ሌላ ተደጋጋሚ መሥዋዕት አስፈላጊ አይደለም::[14]

### 3ለ የካህኑ ተግባር

በሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት በካህኑ ቅዳሴ ጸሎት ኅብስቱና ወይኑ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደምነት ይለወጣሉ ይህም "Sacerdotalism" ይባላል:: ሉተር

---

9 José L. Brandrés Urdániz, *A Glance Behind The Curtain.* Master Printing Press, Ethiopia, Adigrat, 2008, P. 104-5
10 R.L. Dabney, *Systematic Theology* The Banner of Truth Trust, Pennsylvania, U.S.A. 1985, P. 807
11 Louis Berkhof, *Systematic Theology* The Banner of Truth Trust, Pennsylvania, U.S.A. 1994, P. 652
12 Millard J. Erickson, *Christian Theology* Baker Book House G.R. Michigan, 1993, P. 1118
13 Ibid, P. 1118
14 Ibid, P. 1117

ይህን አስመልክቶ፤ ሥርዐቱን ተገቢ የሆነ ሹመት ያለው ካህን ማስፈጸም ያለበት ቢሆንም የክርስቶስ ሥጋና ደም በኅብስቱና ወይኑ ውስጥ መገኘት ከካህኑ ተግባር የተነሣ ሳይሆን ከክርስቶስ ኀይል የተነሣ ነው የሚል አመለካከት ነበረው::[15]

### 3ሀ የዝዊንግሊ አመለካከት (መታሰቢያነት) Symbolic Commemoration / Memorialism

በወንጌል አማኝ ከነበሩት ውስጥ ሉተር በጌታ ራት ላይ የሰጠውን ሐሳብ የተቃወመው በስዊዘርላንድ ውስጥ ተነሥቶ የነበረው የተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪ አልሪክ ዝዊንግሊ (1484-1531) ሲሆን በእርሱ አመለካከት:-

1ለ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማኙ በመዳኑ የተቀበላቸው፣ ክርስቶስ ለፈጸመለት ሥራ የጸጋ ምልክቶችና ማኅተሞች እንጂ ጸጋን የመቀበያ መንገዶች አይደሉም:: ዝዊንግሊ ይህን ሥርዐት በአማኙና በክርስቶስ መኻል ያለውን ግንኙነት በሚያትመው የጋብቻ ቀለበት ይመስለዋል[16]

2ለ የጌታ ራት ራሱ ክርስቶስ እንደተናገረው የሞቱ የመታሰቢያ ሥርዐት ብቻ ነው

3ለ ክርስቶስ በቍርባኑ ላይ በሁለንተናው አይገኝም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ በአሁኑ ጊዜ በሰማያት ስለሚገኝ፤ አንድ አካል በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ በሆነ ቦታ ሊገኝ አይችልም ነገር ግን ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ ስለሆነ በሥርዐቱ ላይ በመንፈሱ ይገኛል[17]

4ለ የሥርዐቱ ጠቀሜታ በክርስቶሰ ሞት የሚገኘውን ጥቅም በእምነት ለመቀበል ነው::

### 4ሀ የካልቪን ወይም የተሐድሶ አመለካከት Spiritual or Reformed

ጆን ካልቪን ከካቶሊኮች፣ ከሉተርና ከዝዊንግሊ ለየት ያለና መካከለኛ ሊሆን ይችላል ያለውን አመለካከት ለማቅረብ ሞክሯል:: በእርሱ አመለካከት:-

1ለ ክርስቶስ በቍርባኑ ላይ በእውን ይገኛል፤ ሆኖም ግን በአካል ሳይሆን በመንፈስ ነው የሚገኘው:: ይህ የካልቪን አባባል ዝዊንግሊ ካቀረበው አመለካከት ጋር ተመሳሳይና ልዩነቱንም ለማውጣት እጅግ አስቸጋሪ ነው:: ካልቪን ይህን አባባሉን ለማስረዳት ጸሓይን እንደ ምሳሌ በመውሰድ ይጠቀማል፤ ጸሓይ ምንም በሰማይ ላይ ብትሆንም፣ ሙቀቷና ብርሃኗ ምድርን እንደሚሸፍኑ የመንፈስ ቅዱስም ነፀብራቅ ለእኛ በክርስቶስ ሥጋና ደም የሚገኘውን ኅብረት ያስተላልፍልፍናል ብሏል::[18]

2ለ በእምነት ለሚካፈለው አማኝ የእግዚአብሔር ማኅተምና ምልክት ነው

3ለ ሉውስ በርክሆፍ የጌታ ራት የወንጌሉ በረከት እና የኪዳኑ ተስፋ በሙሉ በመለኮታዊ ስጦታ የእነርሱ መሆኑን በማረጋገጥ ለአማኞች የክርስቶስን ፍቅር ያትምላቸዋል ይላሉ::[19]

4ለ ቍርባኑን በእምነት ለሚቀበለው አማኝ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው የድነት ጸጋ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ይቀርብለታል

[15] Ibid, P. 1117
[16] Schaff, P., & Schaff, D. S.*History of the Christian church.* Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor, 1997§ 27
[17] Ibid, § 111
[18] John Calvin, *Institutes of the Christian Religion,* Book 4, Chapter 17, Section 12
[19] Berkhof, Systematic Theology, P. 651

5ለ ካልቪን በቍርባኑ ላይ ደሙ ያለውን ምልክትነት አስመልክቶ ሲናገር፤ በበረሃ ለእስራኤላውያን ከዐለት የፈለቀው ውሃ ከነበረው ምልክትነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነው ብሏል::[20]

6ለ የቍርባኑ ጠቀሜታ የሚወሰነው በወሳጁ የእምነትና የተቀባይነት ሁኔታ ላይ ነው::

## 5ሀ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህር

በይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ መሠረት ሁሉም አባል የጌታን ራት አይወስድም:: ይህን ራት መውሰድ የሚችሉት "ቅቡዐን" ወይም "ታናሹ መንጋ" በሚል መጠሪያ የሚጠሩት አንድ መቶ አርባ አራት ሺሆቹ ብቻ ናቸው:: በእነርሱ እምነት እነዚህ ብቻ ናቸው ዳግም የተወለዱት እና በሰማይም ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም የሚኖሩት:: በእነርሱ አመለካከት እነዚህ ለዘላለም ሕይወት ትንሣኤን የሚያገኙ ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ በምድር ላይ ለዘላለም ለመኖር በማይሞት አካል ይነሣሉ::

የይሖዋ ምስክሮች ይህን ሥርዐት የሚፈጽሙት በዓመት አንድ ጊዜ የአይሁድ ፋሲካ በሚከበርበት ቀን (በኒሳን ወር በ14ኛው ቀን) ሲሆን፤ በያሉበት በትላልቅ አዳራሾች ውስጥ ተሰብስበው ጽዋው ከአንዱ ወደ ሌላው ይተላለፋል፤ ሆኖም ሥርዐቱን የሚፈጽሙት ቅቡዐን የሆኑት ማለትም ከመቶ አርባ አራት ሺህ ቍጥር ውስጥ ያሉት ብቻ ናቸው::

## 6ሀ በሞርሞን እምነት ተከታዮች አስተምህር

የሞርሞን እምነት ተከታዮች (Latter day Saints) የጌታን ራት ካቶሊክና ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚጠቀሙበትን (Sacrament) የሚል ቃል በመጠቀም እንደ አንድ የተቀደሰ ሥርዐት ይቀበሉታል::

በሞርሞኖች አስተምህሮ መሠረት የጌታ ራት በጥምቀት ወቅት የሚከናወነው ኪዳን ሕዳሴ ሲሆን፣ ሥርዐቱም ጠቀሜታ የሚኖረው ለተጠመቁና በጥሩ የመንፈሳዊ ሕይወት አቋም ላይ ላሉ አማኞች ብቻ ነው:: ሆኖም ግን ያልተጠመቁና እምነቱን የሚከተሉ ሰዎች እንደዚሁም ሕፃናት[21] ወደፊት ሊጠመቁ ያለውን ጥምቀት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሥርዐቱን ሊወስዱ ይችላሉ::

በቅዳሴ ጸሎቱ አማካይት አንድ አማኝ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም በማስታወስ ኅብስቱና ወይኑን ይወስዳል:: ሞርሞኖች የጌታ ራት ለኀጢአት ሥርየት የሚቀርብ ልመና እና አማኙ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ያለውን ውሳኔ በየሳምንቱ የሚያድስበት ሥርዐት መሆኑን ያምናሉ:: በሥርዐቱም ወቅት የክርስቶስ ሁለንተናዊ መገኘትን የማይቀበሉ ሲሆን ኅብስቱና ወይኑንም የክርስቶስ ሥጋና ደም ትእምርቶች ናቸው የሚል አመለካከት አላቸው::

[20] Calvin, *Institutes of the Christian Religion,* Book 4, Chapter 17, Sections 1, 5.
[21] በሞርሞኖች እምነት የሚጠመቁት ከስምንት ዓመት በላይ የሆናቸው ብቻ ናቸው

የሞርሞኖችን የጌታ ራት ሥርዐት አፈጻጸም አስመልክቶ ለየት ያለው ነገር "Doctrine and Covenants" በተባለው መጽሐፋቸው መሠረት የደሙ ምሳሌ የሆነውን ወይን ሲያዘጋጁ በወይን ፈንታ ውሃን መጠቀማቸው ነው።[22]

## 3.2 ስለ ጌታ ራት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን

### 1ሀ ጠቀሜታው

#### 1ለ ለማስታወሻነት

በ1ቆሮ 11፥26 ላይ እንደምናነበው የሥርዐቱ አንዱ ጠቀሜታ ክርስቶስ ለኀጢአታችን ዋጋ ለመክፈል በእኛ ምትክ ተውላጣዊ ሞት (Substitutionary death) መሞቱን ዳግም እስኪመለስ (ዮሐ 14፥1-4) ድረስ ለማስታወስ ነው።

አማኞች ይህን ሥርዐት በፈጸሙ ቍጥር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ ድረስ እርሱ ያደረገላቸውን ከማስታወስ ባሻገር፤ ለወደፊት አማኞች በክርስቶስ መንግሥት የታላቁ ሠርግ ራት ተካፋዮችና የመንግሥቱ ዜጎች እንደሆኑ በማሰብ ያን ቀን በናፍቆት እንዲጠባበቁ ይረዳቸዋል።

#### 2ለ ለኅብረት መግለጫ

የጌታ ራት ሥርዐት አማኞች በቅድሚያ ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ኅብረት የሚገልጹበት ሥርዐት ሲሆን፤ ይህንንም ከአንዱ ኅብስት በመካፈልና ከአንዱ ጽዋ በመጠጣት ይገልጻሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ኅብረት አስመልክቶ በ1ቆሮ 12፥12-26 ላይ በስፋት ለማብራራት እንደሞከረው አማኞች በሙሉ የአንዱ የክርስቶስ አካል የተለያዩና እርስበርሳቸውም የሚፈላለጉ እንደዚሁም አንዱ ሌላውን የሚያሟላና አንዱ ያለ ሌላው ምሉዕ የማይሆኑ የአንድ አካል ብልቶች ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ ከአንዱ ኅብስት በመውሰድና ከአንዱ ጽዋ በመጠጣት አማኞች በአንዱ አካል በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ አንዱ የሌላው ብልት መሆኑንና እርስበርሳችንም በክርስቶስ ኅብረት እንዳለን የምንገልጽበት ሥርዐት ነው።

#### 3ለ የክርስቶስን ሞት ለማወጅ

“ይህን እንጀራ በምትበሉበት ጊዜ፣ ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ።” 1ቆሮ 11፥26

ሥርዐቱን የሚፈጽመው አማኝ በሙሉ ክርስቶስ ዳግም በክብር እስከሚመለስ ድረስ የክርስቶስን ሞት ይናገራል። “መናገር” የሚለው ቃል በእናት ቋንቋው በግሪክ “καταγγέλλετε” (katagēlete) በሚለው ቃል የተጠቀሰ ሲሆን ትርጕሙም ማወጅ፣

[22] Wickipedia, The Free Encyclopedia

መስበክ፣ ወይም ዘገባ ማቅረብ ማለት ነው፡፡[23] ስለዚህ ይህን ሥርዐት የሚፈጽም አማኝ በሙሉ ጌታ ዳግም እስኪመጣ ድረስ በእርግጥ ክርስቶስ እንደሞተለት ያውጃል፡፡

የክርስቶስ ሞት

- ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የኀጢአት ዕዳ መክፈል
- የኀጢአታችን ቀንበር መሰበርና ከኀጢአት ባርነት ነፃ መውጣታችንን
- ከሕግ ወደ ጸጋ አሠራር መሸጋገራችንን
- ከእግዚአብሔር ጋር መታረቃችንን
- ከኵነኔ ነፃ መውጣታችንን
- የሞት መሸነፍ አዋጅ
- የእነዚህንና የሌሎች የሞቱ ውጤቶች ብሥራት ነው

**4ለ የፍቅር ጥሪ ነው**

አማኞች እግዚአብሔር እንደ ወደዳቸው እነርሱም ደግሞ አንዱ ሌላውን መውደዱን አብሮ ማዕድን በመቍረስ የሚያሳይበት ሥርዐት ነው፡፡

በአይሁድ ባሕል መሠረት ሰዎች አብረው መብልን የሚበሉት እንግዳ ተቀባይነትን፣ ወዳጅነትንና ኅብረትን ለመግለጽ ነበር፡፡ ለምሳሌ በዘፍ 31፥54 ላይ ያዕቆብና ላባ እርቅ ካደረጉ በኋላ ሥርዐቱ በመሥዋዕትና ማዕድ አብሮ በመቍረስ ነበር የተጠናቀቀው፡፡ ተራ በሆነውም ማዕድ ቢሆን አይሁዳዊው አባ ወራ ከእንጀራው በእጁ በመያዝ "እንጀራን ከምድር የምትሰጥ የዓለም ንጉሥ የሆንህ ጌታ አምላካችን ሆይ አንተ የተባረክህ ነህ፡፡" በማለት እግዚአብሔርን ካመሰገነ በኋላ ከእንጀራው ትናንሽ ቁራሾችን በማዕዱ ዙሪያ ላሉ ተመጋቢዎች ይሰጥ ነበር፤ ይህም ተመጋቢዎቹ በሙሉ ከባርኮቱ ተካፋዮች እንደሆኑ ያስገነዝባቸዋል፡፡[24]

ስለዚህ ይህን ራት መካፈል ሥርዐቱን ከመፈጸም ባሻገር አማኞች በአምላካቸው ፊት በአንድ ማዕድ ላይ ተቀምጠው ከአንድ ኅብስትና ከአንድ ወይን በመካፈል በክርስቶስ ያላቸውን ቤተሰባዊ ፍቅር፣ አንዱ ሌላውን እንደ አካሉ በማየት እንደ አካል ብልቶች አብረው አካሉን ለማሟላትና ተባብረው ለመሥራት ያላቸውን ሐሳብ የሚገልጹበት ቀን ነው፡፡

**5ለ ራስን የመመርመርና የዝግጅት ጥሪ ነው**

ይህን ሥርዐት ለመካፈል የሚያስቡ አማኞች ሁሉ በየወቅቱ፣ በግል ከጌታ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና እርስበርሳቸውም ያላቸውን መንፈሳዊ ግንኙነት የሚመረምሩበትና እርማቸውን አስወግደው ለተሻለ መንፈሳዊ ሕይወት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጥሪ ነው፡፡

---

[23] Swanson, J. *Dictionary of Biblical Languages with Semantic Domains : Greek (New Testament)* . Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor 1997 # 2859

[24] Marshal, P. 19

በ1ቆሮ 11፥28 ላይ ጳውሎስ “ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ከመብላቱና ከዚህ ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት፣ ራሱን ይመርምር” ብሏል፡፡ በዚህ የጳውሎስ አነጋገር ውስጥ “ይመርምር” የሚለው ቃል በግሪኩ “δοκιμαζέτω” (*dokimazetō*) በሚል ቃል የተጠቀሰ ሲሆን ትርጒሙም መፈተን፣ መመርመር፣ የአንድን ነገር ትክክለኛነት ማጣራት ማለት ነው፡፡[25] እውቁ የግሪክ ምሁር ሮበርትሰን ይህን ሲያብራሩት “በዚህ ቦታ ራሱን የሚመረምረው ግለሰብ ልክ የአንድን ብረት እውነተኛነት ለማረጋገጥ እንደሚመረምር አድርጐ ነው”[26] ብለዋል፡፡

የጌታን ራት የሚወስዱ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋርም ሆነ ከወንድሞቻቸውና ከእኅቶቻቸው ጋር ያላቸውን መንፈሳዊ ግንኙነት በሚገባ መርምረው፣ ይህን ሥርዐት ለመፈጸም ብቃት ካላቸው ነው መውሰድ ያለባቸው፡፡ በ1ቆሮ 11፥27 ላይ “እንግዲህ ማንም ሳይገባው፣ ይህን እንጀራ ቢበላ ወይም የጌታን ጽዋ ቢጠጣ፣ የጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ[27] ይሆናል፡፡” ይላል፡፡ በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ “ሳይገባው” የሚለው ተውሣከ ግስ በግሪክኛው “ἀναξίως” (*anaxiōs*) ሲሆን በማይመጥን ወይም ብቃት በሌለው ሁኔታ ማለት ነው፡፡[28] ስለዚህ ይህን ሥርዐት የሚካፈሉ በሙሉ ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው ሥርዐቱን መፈጸም አለባቸው፡፡

**6ለ በክርስቶስ ደም የተቋቋመውን አዲስ ኪዳን የመቀበል ምልክት ነው**

ይህን ሥርዐት የሚካፈሉ አማኞች በክርስቶስ ደም የተቋቋመው የአዲሱ ኪዳን ተቀባዮች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ “የአዲስ ኪዳን ደም” የሚለው ሐረግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰሙነ ሕማማቱ በዕለተ ሐሙስ ያደረገውን ቃል ኪዳን የሚያመለክት አነጋገር ነው፡፡ ይህ የቃል ኪዳን ሥርዐት በወቅቱ ለነበሩት አይሁዳውያን ደቀ መዛሙርት የሚሰጠውን ያህል ትርጒም የጥንቱን የቅርብ ምሥራቅ የቃል ኪዳን ሥርዐት ጠንቅቀን ለማናውቀው ለዛሬ ሰዎች አይሰጠንም፡፡ በጥንቱ የቅርብ ምሥራቅ ባሕል መሠረት ሦስት ዐበይት የቃል ኪዳን ሥርዐቶች የነበሩ ሲሆን በተዋረድ የደም፣ የጨውና የጫማ በመባል ይታወቃሉ፡፡

1) የጫማ ቃል ኪዳን በሁለት ሰዎች መካከል ለተከናወነ ጊዜያዊ ስምምነት ቃል የገባው ወገን ቃሉን እንደሚጠብቅ ለማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ጫማውን እንደ መያዣ የሚሰጥበት ሥርዐት ሲሆን፤ ቃሉንም ሲፈጽም ጫማው ይመለስለታል (ሩት 4፥7-8)፡፡ እንደዚሁም ቃል የሚገቡት ሁለቱም ሰዎች ከሆኑ ጫማቸውን በመለዋወጥ ይከናወናል (ዘዳ 25፥10)፡፡

2) የጨው ቃል ኪዳን በሁለት ቃል ተገባቢዎች መካከል የሚከናወን ከጫማ ቃል ኪዳን ይልቅ ጠበቅ ያለ ቃል ኪዳን ነው፡፡ ስምምነቱ የሚፈጸመው ሁለቱ ቃል ተገባቢዎች

[25] Thomas, R. L. *New American Standard Hebrew-Aramaic and Greek dictionaries: Updated edition* . Foundation Publications, Inc.: Anaheim; 1998, 1981 # 1381a

[26] Robertson, A. *Word Pictures in the New Testament* by Sunday School Board of the Southern Baptist Convention. Logos Research Systems: Oak Harbor 1997. (1Cor. 11:28)

[27] “ባለዕዳ” የሚለው ቃል ሮበርትሰን እንዳብራሩት ተጠያቂነትን፣ ተከሳሽትንና በሕግ ፊት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘን የሚያመለክት **ἔνοχος** (***enochos***) በሚለው የግሪክ ቃል የተጠቀሰ ቅጽል ነው፡፡

[28] Swanson, J. *Dictionary of Biblical Languages with Semantic Domains: Greek (New Testament)* . Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor; 1997 # 397

ከኮረጆአቸው ውስጥ ካለው ጨው[29] አንድ እፍኝ በመለዋወጥ እና ከራሳቸው ጨው ጋር በማቀላቀል ሲሆን፤ አንደኛው ወገን ግዴታውን ለማፍረስ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከፍሎ

ከሌላኛው ኮረጆ ውስጥ የራሱን የጨው መጠን አውጥቶ እስኪወስድ ድረስ ቃል ኪዳኑ የጸና ነው።[30]

3) የደም ቃል ኪዳን ከላይ ከተጠቀሱት ከሁለቱም እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሲሆን ቃል ኪዳኑም መሠረት ያደረገው ሕይወት በደም ውስጥ መሆኑን ነው። ይህ ቃል ኪዳን ሲከናወን ሁለቱ ቃል ተገባቢዎች አንድን እንስሳ ገድለው ሁለት ቦታ በመክፈል እጅ ለእጅ ተያይዘው ቃል እየተገባቡ ለሁለት በተከፈለው እንስሳ መኻል ያልፋሉ። በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ቃል ያፈረሰው ወገን ለሞተው እንስሳ ሕይወት መስጠት ስለማይችል ሕይወቱን ይከፍላል። ስለዚህ ቃል ኪዳኑ ፈጽሞ ሊፈርስ አይችልም (ዘፍ 15፥1-21)።[31]

## 2ሀ ሥርዐቱን አስመልክቶ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው እውነቶች

### 1ለ ሥርዐቱን ማቃለል አይገባም

ጌታ በሐዲስ ኪዳን ለአማኞች ከሰጣቸው ሁለት ሥርዐቶች ከጥምቀት ቀጥሎ ያለ ትእዛዝ ስለሆነ ሥርዐቱን ለማስታወሻ ብቻ ነው በማለት ጠቀሜታውን ማሳነስ አይገባም።

ይህ ሥርዐት በመሠረቱ አማራጭ ሳይሆን ትእዛዝም እንደመሆኑ መጠን፣ ይህን ሥርዐት መፈጸም የማንኛውም አማኝ ግዴታ ነው። ከላይ በጠቀሜታው ውስጥ እንደተገለጸው ሥርዐቱን ለመፈጸም አማኞች የሚያደርጓቸው የክርስትና ሕይወታቸውን እንዲያስተካክሉ የሚረዷቸው፣ ከእግዚአብሔርና ከሌሎችም የክርስቶስ ቤተሰቦች ጋር ያላቸውን መንፈሳዊ ግንኙነት እንዲያስተካክሉ የሚያደርጓቸው ዝግጅቶች አሉ፣ ሥርዐቱን በመፈጸም ደግሞ የሚያስታውሱት በክርስቶስ የተፈጸመላቸው ከፍተኛ ውለታ አለ፣ የሚመሰክሩት እውነት አለ፣ የሚተገብሯቸው ክርስቲያናዊ ምግባራት አሉ። ከዚህም በተጨማሪ ሥርዐቱን መፈጸም ለአማኞች የክርስቶስን ዳግም ምጽአት አስመልክቶ የሚነገራቸው ትልቅ እውነት ስላለ ይህን ሥርዐት ለማስታወሻነት ብቻ ነው ብሎ ጥቅሙን ማሳነስና ማቃለል አይገባም።

### 2ለ ሥርዐቱ ሲፈጸም ጥንቃቄ ያስፈልጋል

ለሥርዐቱ የሚሰጠው ትርጉም በማስታወሻነቱ ላይ ብቻ ካተኮረ አንዳንድ አማኞች በንቀት ተደፋፍረው ሥርዐቱን የሚፈጽሙ ከሆነ ፍርድ ሊያስከትልባቸው ይችላል። 1ቆሮ 11፥27-31 "እንግዲህ ማንም ሳይገባው፣ ይህን እንጀራ ቢበላ ወይም የጌታን ጽዋ

[29] በእስራኤል ለምግብ ማጣፈጫነትና በበረሃው ምክንያት ለሚባክነው ሰውነት ውስጥ የሚገኝ የጨው መጠን ማሟያ እያንዳንዱ ሰው የተወሰነ ጨው በኮረጆው ውስጥ ይይዝ ነበር።
[30] George P. Koshy, *The Lord's Table & The Lord's Supper* Logos Media, Mulanthuruthy, India, P. 28
[31] M. S. Mills, *The Life of Christ : A study guide to the Gospel record. Three volumes*: 3E Ministries: Dallas, 1999 P. 239 - 242

ቢጠጣ፣ የጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ ይሆናል።...ከእናንተ መካከል ብዙዎች የደከሙትና የታመሙት አንዳንዶችም ያንቀላፉት በዚህ ምክንያት ነው። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብን ነበር።" ይላል። ይህ አነጋገር የሚያስገነዝበን ምንም የሥርዐቱ ዐቢይ ዐላማ

ለማስወሻነት ቢሆንም ጌታ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዐት እንዲሆን ያዘዘው እንደመሆኑ መጠን መንፈሳዊም ይዘት አለውና አማኞች ይህን ሥርዐት ሲፈጽሙ እንደ ማንኛውም ክርስቲያናዊ አገልግሎት በፍርሃትና በጥንቃቄ ሊያደርጉት ይገባል። ይህን በንቀትና በአክብሮት ማጣት የሚያደርጉ ደግሞ ከጌታ ዘንድ ቅጣትን እንደሚቀበሉ ቃሉ ይነግረናል።

### 3ለ ሥርዐቱን የተለየ ጥቅም ለማግኛ አድርጐ ማሰብ አይገባም

ከላይ የሥርዐቱ ጠቀሜታ በተብራራበት ክፍል ውስጥ በስፋት እንደተጠቀሰው የሥርዐቱ ቀዳማይ ዐላማ ማስታወሻነት ሆኖ፤ ሥርዐቱን ለመፈጸም በሚደረገው ዝግጅትም ሆነ ሥርዐቱን በመፈጸም አማኙ የሚያገኛቸው የተለያዩ ጥቅሞች አሉ። ከዚህ በዘለለ ግን የእግዚአብሔር ቃል ከሚያዘው ውጭ ሥርዐቱን መፈጸም ለድነት እገዛ እንደሚያደርግና የተለየ ጸጋን ከአምላክ ዘንድ እንደሚያሰጥ አድርጐ ማሰብ ቃሉን ከመጣስም ባሻገር የክርስቶስን መሥዋዕትነት ማቃለልም ይሆናል። ክርስቶስ ለሰው ልጆች በሙሉ በመስቀል ላይ የከፈለው ዋጋ ምንም ዐይነት ተጨማሪ አይፈልግም። እንደ ጥምቀትና የጌታ ራት ያሉ በተቋም ደረጃ ያሉትንም ሆነ ሌሎቹን ትእዛዛት የምንፈጽመው የዳነ ሰው ክርስቲያናዊ ግዴታዎች ስለሆኑ ነው እንጂ ለድነታችን የተወሰነ እገዛ ለማድረግ አይደለም።

### 4ለ አማኞች በሙሉ ይህን ሥርዐት እንዲፈጽሙ ማበረታታት ያስፈልጋል

የጌታ ራት ሥርዐት እያንዳንዱ በክርስቶስ አካል ውስጥ የገባ አማኝ ሊፈጽመው የሚገባ ግዴታዊ የሆነ ትእዛዝ ነው።

በአማኙ ሕሊና ውስጥ ከፍተኛ ወቀሳና ክስ፣ እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ላይ ጒዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ አካሉን የሚያረክሱ ግዙፍ እና ተደጋጋሚ የሆኑ የኀጢአት ልምምዶች ካልሆኑ በስተቀር በቀላሉ በንሥሓ ሊታረሙ በሚችሉ ኀጢአቶች ምክንያት አማኞች የጌታን ራት እንዳይካፈሉ መከልከል የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፈው አሠራር ነው። አማኞች እርስበርሳቸው ያላቸውን ያለመግባባትም ሆነ ሌላ ዐይነት ችግሮች መፍታት እንዳለባቸው በማስተማር፣ የዕርቅና የንግግር መድረኮችን በማዘጋጀትና በማማከር አገልግሎት በመታገዝ ችግሮችን መፍታት የእረኞች ቀዳማይ ተግባር መሆን ይኖርበታል። ይህን በማድረግ አማኞች ሁሉ የጌታን ራት የሚወስዱበትን መንገድ ማመቻቸት እንጂ በክልከላው ላይ ብቻ ትኩረት መብዛት የለበትም።

## 3ሀ መወገድ ያለባቸው ኀጢአታዊ አካሄዶች ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮ

### 1ለ መለያየት

አማኞች የአንድ አካል ብልቶች ስለሆኑ 1ቆሮ 12፥12-13 በመካከላቸው ከተለያዩ ኀጢአቶች የሚመነጩ መለያየቶችን ማስወገድና የመንፈስን አንድነት መጠበቅ አለባቸው ኤፌ 4፥3።

ይህ አንድነት ደግሞ ልዩነቶችን በመቀበልና በመቻቻል የሚመጣ እንጂ የግድ አንድ ዐይነት ሐሳብ በማሰብ፣ ተመሳሳይ አስተምህሮን በመከተል የሚገኝ አይደለም:: አማኞች ኅብረት አላቸው ማለት አንድ ዐይነት ናቸው ማለት ሊሆን አይችልም፤ አይገባም:: የእያንዳንዱ አማኝ አመጣጡና መንፈሳዊ አስተዳደጉ የተለያየ እንደመሆኑ መጠን ያንን አቻችሎ ኅብረትን መፍጠር በጌታ የማደግ ውጤት ሲሆን፤ መለያየትን በፈቃደኛነትና በፍቅር በተለያየ አቅጣጫ ለማገልገልና ለመብዛት እንጂ ለመጠላላት አድርገው የሚወስዱ አማኞች የጌታን ራት ዓላማ የሚጻረር ኀጢአት እየሠሩ ስለሆነ ችግራቸውን ማረም ይኖርባቸዋል::

### 2ሰ የራቱን ዐላማ መሳት

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሌሎችም አብያት ክርስቲያናት ውስጥ ልማድ እንደነበረው ሁሉ (ሐዋ 2፥42, 46) አማኞች በሙሉ በአንድነት "የፍቅር ማዕድ" በሚል ስያሜ ይጠራ የነበረውን ማዕድ ከጌታ ራቱ በፊት ይቆርሱ ነበር:: ሆኖም በቆርንቶስ የነበሩ ገንዘብ ያላቸው አማኞች ድኾቹን ሳይጠብቁ አስቀድመው የራሳቸውን ራት ከሚመስሏቸው ጋር ብቻ ተሰብስበው ከሥርዐቱ በፊት ይበሉ ነበር[32]፤ አንዳንዶቹም ይሰክሩ ነበር (1ቆሮ 11፥21)::

ይህንንም በማድረግ ድኾቹ በእግዚአብሔር ላይ እንዲያማርሩና በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ያልነበረው የባዕድነት መንፈስ እንዲሰማቸው በማድረጋቸው እግዚአብሔርን አሳዝነው ነበር:: የራቱ ዐላማ አንድነትና ኅብረት ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን መለያየትና መከፋፈል ባለበት ሁኔታ ሥርዐቱን ለይስሙላ ይወስዱ ነበር፤ ይህ ደግሞ የራቱን ዐላማ መሳት ይሆናል:: ዛሬም ቢሆን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ይህ ሁኔታ በእጅጉ የሚታይ ሲሆን፤ የሥርዐቱን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት (ከአማኙ የሚጠበቅበትን) ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ሰዎች ይህን ሥርዐት የቤተ ክርስቲያን አንድ ሥርዐት እንደመሆኑ ብቻ በማሰብ ሲፈጽሙ ይስተዋላል:: ይህ ደግሞ በቆሮንቶስ እንደታየው የሥርዐቱን ዐላማ መሳት ነው::

### 3ሰ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መናቅ

ጳውሎስ በ1ቆሮ 11፥22 ላይ "...ወይስ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በመናቅ፣ምንም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን?" በማለት ይህ ድርጊታቸው ከንቀትና ከማናለብኝነት የመነጨ እንደነበር ገልጧል::

በዛሬይቱም ቤተ ክርስቲያን በጌታ ቤት ብዙ ከመኖርና የእግዚአብሔርን ምሕረት ከመለማመድ የተነሣ የሚፈጸሙ የድፍረት ኀጢአቶች መታረም ይገባቸዋል:: ሥርዐቱን አስፈጻሚው ፍጥረታዊ የሆነ ሰው፣ ሥርዐቱም የሚፈጸመው ሰው በሠራው ቤተ መቅደስ

ውስጥ ቢሆንም ሥርዐቱ ግን መንፈሳዊና በክርስቶስ የተደነገገ ስለሆነ ከድፍረት ኀጢአት መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: በአንድ መልኩ የራቱን ዐላማ በመሳት ሥርዐቱን እንደ ተራ የቤተ

[32] Wiersbe, W. W. *The Bible Exposition Commentary*. "An exposition of the New Testament comprising the entire 'BE' series"--Jkt. Victor Books: Wheaton, Ill. 1996; (1Cor. 11:21)

ክርስቲያን ትእዛዝ በመቊጠር ያለ ምንም ዝግጅት ሥርዐቱን የሚካፈሉ፣ በብዙ የኀጢአት ልምምዶች ውስጥ ተዘፍቀው ያለ ምንም ፍርሃት ሥርዐቱን የሚፈጽሙ አማኞች ያሉ ሲሆን፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ሥርዐቱን በመናቅ በሥርዐቱ ላይ የማይገኙ አማኞችና አገልጋዮች አሉ። በድፍረት ሥርዐቱን የሚፈጽሙትም ሆነ፣ በንቀት የማይካፈሉት ሁለቱም እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ አማኞች ናቸው። በዮሐ 14፥15 ላይ ጌታ "ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ" ሲል ማንኛውም አማኝ ከዳነ በኋላ ጌታን መከተሉና መውደዱ ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱ በቃሉ የተጻፉትን ትእዛዛቱን መፈጸም እንደሆነ ለመግለጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅርና መገዛት የሚታየው ለእርሱ መልካም የሆነን መሥዋዕት ስናቀርብ ነው። ስለዚህ መታዘዝ ግዴታችን ሲሆን ከታዘዝን ደግሞ ለይስሙላ ሳይሆን አግባብ ባለው መልኩ መስፈርቱን አሟልተን መሆን ይኖርበታል።

## 3.3 ሥርዐቱን የሚፈጽሙ አማኞች የዕድሜ ገደብ

ይህ ጉዳይ ሥርዐቱ የሚውለው ለመታሰቢያነት ነው የሚለውን የዝዊንግሊ አስተምህሮ ለሚከተሉ አብዛኞቹ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ብዙም ችግር አይደለም። በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ድንጋጌ የጌታን ራት ሥርዐት የሚካፈለው የጥምቀትን ሥርዐት የፈጸመ አማኝ ብቻ ነው፤ የሚጠመቁትም ለአቅመ አዳም ወይም ሔዋን የደረሱና ጌታን ለመከተል ያላቸውን የግል ውሳኔ ራሳቸውን ችለው ማሳወቅ የሚችሉ ብቻ ናቸው። ስለዚህ ዕድሜአቸው ደርሶ የተጠመቁ ሁሉ ሥርዐቱን ይፈጽማሉ።

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ግን ወንዶች በ40፣ ሴቶች በ80 ቀን ሲጠመቁ ምንም ኅብስቱን ለመውሰድ ባይችሉም ከወይኑ በሕፃናቱ አፍ ውስጥ ተደርጐላቸው ከቍርባኑ ይካፈላሉ። በመቀጠልም ወላጅ እንዲቆርቡ ከፈቀደላቸው የዕድሜ መጠን አንስቶ እስከ ሞት ድረስ ይህ ሥርዐት በማንኛውም አማኝ ክርስቲያን ይፈጸማል። በኦርቶዶክስ እምነት በቅዳሴ ጸሎትና በቃሉ አማካይነት ኅብስቱና ወይኑ በቀጥታ ወደ ጌታ ሥጋና ደምነት ስለሚለወጡ ያን መብላትና መጠጣት የኀጢአት ሥርየት ለማግኘትና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ለማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ እስከ ሞት ድረስ ይህን ይፈጽማል።[33]

ይህን አስመልክቶ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ዮሐ 6፥53ን መሠረት በማድረግ ሕፃናት እንዲቆርቡ ስታደርግ፤ ከዚህ በተቃራኒ የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን 1ቆሮ 11፥28-29ን መሠረት በማድረግ ሥርዐቱ ራስን መመርመርን ያካተተ ስለሆነ ሕፃናት እንዳይወስዱ ከልክላለች።[34]

## 3.3 የጌታ ራት የሚሰጥበት የጊዜ ርዝመት

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በሐዋ 2፥46 ያለውን በመጥቀስ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የጌታ ራት ሥነ ሥርዐት በመጀመሪያ በየቀኑ ይደረግ ነበር የሚል እምነት ያላቸው ሲሆን፤

---

[33] *ዓሥራት ገብረ ማርያም ትምህርተ መለኮት* (ሦስተኛ እትም) አዲስ አበባ፣ 1994፣ ገጽ 179

[34] Schaff, P., & Schaff, D. S.. *History of the Christian Church*. Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor, WA; 1997; § 97

በአብዛኛው ግን ከቃሉም እንደምንረዳው በሳምንት አንድ ቀን ማለትም ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን (ሐዋ 20፥7) ይከናወን ነበር።[35]

ሥርዐቱ በሳምንት አንድ ቀን ያለ ምንም ማቋረጥ ይደረግ እንደነበር ሁሉም የታሪክ ምሁራን የሚስማሙበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ግን በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አፈጻጸሙ የተለያየ ነበር። አውግስጢኖስ "የጌታ ራት የዕለት እንጀራችን ነው" የሚል እምነት ስለነበረው ይህን ለአማኙ ለራሱ ቢተውለት ይሻላል የሚል አመለካከት ነበረው። ባስልዮስ በሳምንት አራት ቀን ያከናውን ነበር። ገናድዮስ ዘምስንያ ደግሞ በሳምንት አንድ ቀን ቢደረግ መልካም ነው የሚል አመለካከት ነበረው።[36] ሆኖም ግን በምሥራቁ ዓለም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ከአራተኛው ምዕተ ዓመት በኋላ በዓመት አንድ ቀን እና በታላላቅ በዓላት ላይ ብቻ ይደረግ እንደነበር የሚጠቁሙ ማስረጃዎች አሉ።[37]

ሥርዐቱ በየስንት ጊዜው ይፈጸም የሚለውን ነገር አስመልክቶ ሐዲስ ኪዳናችን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ያደርጉ የነበሩበትን ቀን ከመጠቆም ውጪ የደነገገው ልዩ ትእዛዝ ስለሌለ የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ብትችል የጥንቱን ልማድ በመከተል እንደማንኛውም የአምልኮ ሥርዐት በሳምንት፣ አለያም አሁን በተለያዩ ቦታዎች እየተደረገ እንዳለው በወር ብታደርገው መልካም ሲሆን፤ ከወር መዝለሉ ግን የሥርዐቱን አስፈላጊነት ስለሚቀንሰው አግባብ አይሆንም።

---

[35] Sell, H. T. *Studies in Early Church History*. Woodlawn Electronic Publishing: Willow Grove, PA Vol. 3, 1998, Page 643
[36] Charles Hodge, *Systematic theology*. Logos Research Systems, Inc.: Oak Harbor, WA 1997;Vol. 3, Page 643
[37] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 643